# የግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነትን ለመወሰን የወጣ ረቂቅ አዋጅ

## አጭር ማብራሪያ

ነሃሴ 2014 ዓ/ም

## መግቢያ

ግብርና በኢትዮጵያ የልማት ፖሊሲዎች እና ስትራቴጅዎች ልዩ ቦታ የያዘ ዘርፍ መሆኑ ይታወቃል። ከግብርና መር ኢንዱስትራያላይዜሽን ፖሊሲ እስከ እድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ሁሉም የሀገሪቱ የልማት ፖሊሲዎች ገጠርንና ግብርናን ማዕከል ያደረጉ ናቸው። በተለይም የሁለተኛው እድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ግብርናን መሠረት አድርጎ በአጠቃለይ ኢኮኖሚው ላይ መዋቅራዊ ለውጥ በማምጣት እ.ኤ.አ በ 2025 ኢትዮጵያን መካከለኛ ገቢ ካለቸው ሀገራት ተርታ ለማሰለፍ ያለመ ሰፊ የልማት አጀንዳ ነው። የታቀደውን አጠቃላይ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣትም አነስተኛ ይዞታ ባላቸው አርሶ/ አርብቶ አደሮች ላይ የተመሠረተውን ግብርና ወደ ገበያ ተኮር ማሸጋገር እንደሚያስፈልግ የሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በግልፅ ያስቀምጣል። በዚህም ግብርናው አገራዊ የምግብ ፍላጎትን ከማሟላት ባሻገር በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ የሆኑ የኤክስፖርት ምርቶችን በብዛትና በጥራት በማቅረብ፣ ለኢንዱስትሪው ዘርፍ ጥሬ ዕቃ በማቅረብና እና ለኢንዱስትሪ ምርቶች ገበያን በመፍጠር ቁልፍ ሚና እንዲጫወት ይጠበቃል።

## የግብርና ምርት ውል ፋይዳ

አጠቃላይ እንደ ሀገር የግብርናውን ዘርፍ ማዘመን ከሚያስችሉ አሰራሮች መካከል አንዱ የግብርና ምርት ውል (Contract Farming) ነው። ይህም የአርሶ/አርብቶ አደሮችን የማምረት አቅም በማሳደግ ረገድ ፋይዳው የጎላ ነው። ሥርዓቱ ባብዛኛው የመንግስትን ሚና በሚቀንስ መልኩ የሚከናወን በመሆኑ እና በባለሃብቶች መሰረታዊ ፍላጎት የተመሰረተ በመሆኑ ቀጣይነቱ እና ውጤታማነቱ ምንም አያጠራጥርም። በማሳ እና ፍላጎት ካላቸው ኩባንያዎች/አግሮፕሮሰሰሮች ጋር በፍቃደኝነት እንዲተሳሰሩ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ትስስር የሚፈጥሩ ኩባንያዎች የራሳቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ በሚያደርጉት ጥረት አርሶአደሩ ተጠቃሚ ይሆናል። የባለሃብቱ ለጥራትና ብዛት ያለው ምርት ለማግኘት ያለው ፈላጎት አርሶ አደሩን በመደገፍ ተጠቃሚ ሊያደርጉት ይችላሉ። አርሶ/አርብቶ አደሩን ተጠቃሚ ሊያደርጉ የሚያስችሉ አሰራሮችን በቴክኖሎጂ፣ በስልጠና፣ የግብዓት አቅርቦት በተቀላጠፈ ሁኔታ ተደራሽ እንዲሆን ያደርጉታል። በተጨማሪም አርሶ/አርብቶ አደሩ ወደ ዘመናዊ የአሰራር ሂደት እንዲገባ በማድረግ የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ተጠቃሚነታቸው እንዲረጋገጥ ማድረግ ያስችላ። እንዲም ፤ በመንግስት በኩል የሚቀርቡትን የአርሶ/አርብቶ አደሩ ምርትና ምርታማነት ማሳደጊያ ግብአቶች በአስመራቹ በኩል ተደራሽ በማድረግ የመንግስትን ጫና ይቀንሳል። አስመራቹ ትስስር የፈጠረበት አካባቢ ላሉ ማህበረሰብ የተለያዩ ማህበራዊ ድጋፎችን (መንገድ፣ ትምህርት ቤት፣ የህክምና መስጫ ተቋማት) በማድረግ ሰላማዊ የሆነ ኢንቨስትመንትን ማሳለጥን ያረጋግጣል። እንደ ሀገር ከውጭ የሚገቡ የግብርና ምርቶችን በሀገር ውስጥ በማምረት የሀገር ውስጥ የግብርና ምርት ፍጆታ ከማሟላት አልፎ የግብርና ምርቶችን ወደ ውጭ በመላክ የውጭ ምንዛሬ እጥርት ለመቀነስ፤ እንዲሁም በአብዛኞቹ ክልሎች እየተሰሩ ላለው የኢንዱስትሪ ፓርኮች ጥሬ እቃ አቅርቦት ችግርን ከመቅረፍ አንጻር የግብርና ምርት ውል ከፍተኛ ሚና ይጫወታል።

በሌላ በኩል አርሶ/አርብቶ አደሩን ከእጅ ወደ አፍ ከሆነ አመራረት ሂደት ተላቀ የተሻለ ዋጋ ወዳላቸው ምርቶች ወደማምረት እንዲሸጋገር በማድረግ ከምርቱ የሚያገኘው ገቢ እንዲያድግ ማድረግ ለግብርናው ዘርፍ መዋቅራዊ ለውጥ ወሳኝ ነው። ይህንንም ለማድረግ የግብርና ምርት ውል ከፍተኛ ሚና ሊጫዎት እንደሚችል በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፍርሜሽን ዕቅድ ላይ ተመልክቷል።

ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ፤የድህረ-ምርት ብክነትን ለመቀነስ እና አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮችን ከአስተማማኝ ገዥዎች በማገናኘት ጠንካራ የገበያ ትስስር ለመፍጠር የግብርና ምርት ውል ወሳኝ ቢሆንም እስካሁን ባለው ሂደት የመንግስት ክትትልና ድጋፍ እንብዛም አይደለም። ሆኖም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የግብርና ምርት ውል ጥቅምን መረዳት ለመደገፍ ጥረት እየተደረገ ይገኛል።

## የግብርና ምርት ውል ሕግ አስፈላጊነት

ውጤታማ የግብርና ምርት ውል እንዲኖር አጋዥ የሆኑ የሕግና ተቋማዊ ስርዓቶች ሊዘረጉለት ይገባል። በእርግጥ በአምራቹ/አርቢውና በገዢው መካከል የሚኖረው ግንኙነት የውል ግንኙነት እንደመሆኑ መደበኛው የውል ሕግ ግንኙነቱን ሊገዛ ይችላል። ይሁንና ጠቅላላ የውል ሕጎች የተወሰኑ በአምራቹ/አርቢውና በገዢው መካከል የሚኖሩ ግንኙነቶችን ሊገዙ ቢችሉም የግብርና ምርት ውል ልዩ ባህሪያትን ሙሉ በሙሉ ሊያስተናግዱ የሚችሉ አይደሉም። በተለይም አብዛኛው ግብርና አነስተኛ ይዞታ ባላቸው አርሶ/አርብቶ አደሮች በሚከናወንበት አገራችን ራሱን የቻለ ዝርዝር ሕግ መኖሩ ጠቀሜታው የላቀ ነው።

የግብርና ምርት ውልን የተመለከተ የተለየ ሕግ አስፈላጊነትን የሚያጎሉ የተለያዩ ምክንያቶች አሉ። ከበርካታ ምክንያቶች መካከል የግብርና ምርት ውል ተዋናዮችና ባለድርሻ አካላት በርካታ መሆናቸው፣ የግብርና ምርት ውል አሰራር በክልል ውስጥ እና በክልሎች መካከል ባሉ አስመራቶችና አምራቶች መካከል ሊካሄድ መቻሉ፣ በዘርፉ ላይ አለማቀፋዊ የሆኑ ድርጅቶች የመሰማራት ፍላጎት ያላቸው መሆኑ ከሚጠቀሱት መካከል ናቸው። እንደማንኛውም የውል ግንኙነት የግብርና ምርት ውል በዋናነት ተዋዋይ ወገኖችን የሚመለከት ቢሆንም ከተዋዋይ ወገኖች ባሻገር የተለያዩ ባለድርሻ አካላትንም የሚመለከት ጉዳይ ነው። ለምሳሌም መንግስት የውል ግኑኝነቱን ለምርትና ምርታማነት መጨመርና ለግብርና እድገት አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ይፈልጋል። በተጨማሪም መሰረታዊ የገበሬዎች የሕብረት ሥራ ማህበራት የአባላቶቻቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ ይችሉ ዘንድ የራሳቸውን ሚና መጫዎት ይፈልጋሉ። በመሆኑም የግብርና ምርት ውል ከተዋዋይ ወገኖች ባለፈ የተለያዩ የባለድርሻ አካላትን ጥቅሞችና ፍላጎቶች የሚመለከት በመሆኑ ይህንኑ ያገናዘበ ራሱን የቻለ ሕግ ያስፈልገዋል።

የግብርና ምርት ውልን የተመለከተ የተለየ ሕግ የሚያስፈልግበት ሁለተኛው ምክንያት በተዋዋይ ወገኖች መካከል የመደራደር ዐቅም ልዩነት መኖር ነው። በተለያዩ ምክንያቶች ተዋዋይ ወገኖች እኩል የመደራደር ዐቅም ላይኖራቸው ይችላል። በተለይም አነስተኛ ይዞታ ያላቸው አርሶ/አርብቶ አደሮች ከታላላቅ ገዢዎች ጋር እኩል

የሆነ የመደራደር ዐቅም እንደማይኖራቸው ግልፅ ነው። የግብርና ምርት ውልን የተመለከተ እራሱን የቻለ ሕግ መኖር ይህንን የዐቅም ልዩነት በተወሰነ ደረጃ ሊያጠብ ይችላል።

የግብርና ምርት ውልን የተመለከተ የተለየ ሕግ የሚያስፈልግበት ሶስተኛው ምክንያት ደግሞ የግብርና ምርት አመራረት ሂደት ለተለያዩ አደጋዎች የተጋለጠ መሆኑ ነው። ለምሳሌም በአየር ንብረት መለዋወጥ፣ በበሽታ፣ ወዘተ ምክንያት በውሉ መሠረት መፈፀም የማይቻልባቸው ሁኔታዎች ሊፈጠሩ ይችላሉ። በዚህም የተነሳ በተዋዋይ ወገኖች መካከል አለመግባባቶች ሊፈጠሩ ይችላሉ። የግብርና ምርት ውልን የተመለከተ የተለየ ሕግ የግብርና ምርት ልዩ ባህሪያትን ግምት ዉስጥ ያስገባ አለመግባባቶችን የመፍቻ መንገድ በማመቻቸት በተዋዋይ ወገኖች መሀከል ፍትሀዊ ግንኙነት እንዲኖር እና የተረጋጋ የግብርና ምርትና ግብይት እንዲኖር ያስችላል።

አራተኛ የግብርና ምርት ውል እንዲስፋፋ፣እንዲበረታታ እና ለግብርና ምርት ዕድገት አንድ ዋነኛ መሣሪያ እንዲሆን ተቋማዊ ስርዓት እንዲኖረዉ ያስፈልጋል። እራሱን የቻለ ሕግ የግብርና ምርት ውልን በስፋት ለማስተዋወቅ፣ ለማስፋፋትና ለማስተባበር የሚያስችል ተቋማዊ ስርዓትን ለመወሰን ያስችላል።

አምስተኛ እራሱን የቻለ የግብርና ምርት ውል ሕግ መኖር ወጥ የሆነ አሰራር እንዲኖር ያስችላል። አሁን በተግባር የሚታየው ወጥነት የሌለውና የተዘበራረቀ አሰራር ነው። የግብርና ምርት ውልን በወጥነት የሚገዛ ሕግ ባለመኖሩ ተወዋይ ወገኖች በመሰላቸው የውል ግንኙነቶችን ሲያከናውኑ ይታያል። ይህም አሰራር ለውሎች አፈፃፀም አሰቸጋሪ እና ለአለመግባባቶች በር ሲከፍት ይታያል። እራሱን የቻለ የግብርና ምርት ውል ሕግ መኖር ወጥ የሆነ አሰራርን በመዘርጋት ይህንን ችግር ይፈታል።

## በግብርና ምርት ውል ረቂቅ ሕግ ዝግጅት ባለድርሻ አከላትን ስለማሳተፍ

የወጪ ንግድ አስተባባሪ ብሔራዊ ኮሚቴ መጋቢት 14 ቀን 2009 ዓ/ም ባካሄደው ስብሰባ " የአውት ግሮዎርስና ኮንትራት እርሻ በሕግ ማዕቀፍ እንዲደገፍ የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ ጥናት መሠረት ያደረገ ረቂቅ ሕግ እንዲያቀርብ ኃላፊነት ወሰደ። የኤትኤ አማካሪ ቀጥሮ በጥናት መሰረት የተረቀቀው የግብርና ውል ረቂቅ አዋጅ ላይ በህዳር ወር 2010 ዓ.ም በተከታታይ በተዘጋጁ መድረኮች የፌደራልና የክልል ባለድርሻዎች አስተያየት ሰጡበት።ግንቦት 29 ቀን 2010 ለሚመለከታቸው የፌደራል የመንግስት ባለድርሻ አካላት ቀረበ። ግ/ሚ/ር እ/ል/ዘርፍ ጥር/2011 ባደራጀው ኮ/ቴ በኩል ሥነዱ እንዲያጥር እና አሁን ያለውን ይዘት እንዲይዝ ተደረገ። በእንስሳት ልማት ዘርፍ ጠያቂነት ያጠረው የአዋጁ ይዘት የካቲት 30 ቀን 2011 ዓ.ም ቢሾፍቱ ለፌደራልና ለክልል ባለድርሻ አካላት አስተያየት እንደገና ቀረበ። ነሐሴ 8/2012 አዳማ ላይ የፌደሬሽን ም/ቤት ከግብርና ሚ/ር ጋር በቅንጅት ባዘጋጁት አውደጥናት በፌደራል መንግስት የይጽደቅ ይሁንታ ከክልሎች አገኙ።

በአጠቃላይ የፌደራልና የክልል ባለድርሻ አካላትን አስተያየት እንዲሰጡበት ተደረጓል። ከሚመለከታቸው ከፌደራል የፌደሬሽን ም/ቤት፣ የሚኒትሮች ም/ቤት ህግ ክፍል፣ የፌዳል ፍትህ ሚኒስቴር፣ የግብርና ሚኒስቴር፤

ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር፤ ቡናና ሻይ ባለስልጣን፤ የምርት ገበያ ባለስልጣን እና የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ረቂቁ ቀርቦ ተጨማሪ አስተያየቶችን በማሰባሰብ እንዲዳብር ተደርጓል::ከክልል ባለድርሻ አካላት ክልል ም/ቤት ዐቃቢያን ህጎች፣ አፈጉባኤዎች፣ ግብርና ቢሮና ተጠሪ ተቋማት አስተያየት እንዲሰጡበት ተደርጓል። በወቅቱ ረቂቅ አዋጁ በፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ተልኮ አስተያየት የተሰጠበት ሲሆን በፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የተሰጠው አስተያየት በረቂቅ አዋጁ እንዲካተት ተደርጓል።

የሚኒስትሮች ምክር ቤትም በዚህም ጉዳይ ላይ የፌደራል መንግስት ሕግ የማውጣት ስልጣን ስለሌለው አወጁን የፌደራል መንግስት ማወጣት ሥልጣን የለውም ይሁንና ግን በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 55 /6/ መሠረት አንድ የኢኮኖሚ ማኅበረሰብን ለመፍጠር ሲባል በፌደሬሽን ምክር ቤት በኩል በፌደራል መንግሥት ሕግ እንዲወጣላቸው በማስወሰን ማቅረብ የምንችል መሆናችንን በመወሰን መልሶታል።

በዚህም መነሻነት ጉዳዩ ለፌደሬሽን ምክር ቤት ረቂቁ ቀርቦ ምክር ቤቱ በቁጥር ፌደም/አፈ/5/577 ጥቅምት3/2013ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥቷል።

ምክር ቤቱ የግብርና ምርት ውል ረቂቅ አዋጅ የሚመለከታቸውን የክልል ባለድርሻ አካላት ጋር ሰፊ ውይይት አድርጓል። በውይይቱም ረቂቅ አዋጁ ለአርሶ/አርብቶ አደሩ ኑሮ መሻሻል እና ለግብርናው ምርት እድገት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑና አዋጁን በአገር አቀፍ ደረጃ እንዲወጣ ማድረግ ወጥ የሆነ አሠራር ለመፍጠርና ተቋማዊ ሥርዓት ለመዘርጋት ጠቃሚ መሆኑን መግባባት ላይ ተደርሷል። ረቂቅ አዋጁ በዋናነት አንድ በኢኮኖሚ የተሳሰረ ማህበረሰብ ከመፍጠር አኳያ ያለው ሚና ከፍተኛ ከመሆኑም ባሻገር የሀገራችንን የምርት ግብይት በዚህ የምርት ውል ሕግ መሰረት እንዲዘምንና የተፈጠሩ የግብይት ችግሮችን በባለቤትነት ስሜት ከመፍታት አኳያ አገራዊ የግብርና ምርት ውል ሕግ ሆኖ ቢወጣ አገራዊ ፋይዳው ከፍተኛ ይሆናል። ከዚህ ጎን ለጎን አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ከመፍጠር አኳያ የምርት ውል ሕጉ ሊኖረው የሚችለው ፋይዳ የግብርና ምርት እሴት ተጨምሮባቸው ለገበያ ሲቀርቡ በማህበረሰቡ መካከል የቆየውን የኢኮኖሚ ትስስር ያጠናክረዋል።

ስለዚህ በ5ኛ የፓርላማ ዘመን 6ኛ ዓመት 1ኛ መደበኛ ጉባዓው የግብርና መርት አምራችና እስመራች ውል ረቂቅ አዋጁ የፍትሃ ብሄር ጉዳይ መሆኑን፤ አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመፍጠር አስፈላጊ መሆኑን እና አንድ የኤኮኖሚ ማህበረሰብ ከመፍጠር በዘለለ የክልሎችን ሥልጣን የማያጣብብ መሆኑን በማረጋገጥ፣ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በሕገመንግስቱ አንቀጽ 62 (8) እና 55(6) በተሰጠው ሥልጣን መሰረት አዋጅ ሆኖ እንዲፀድቅ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምጽ ወስኗል።

## የአዋጁ ክፍሎችና አንቀጾች ማብራርያ

### 1. <u>የረቂቅ አዋጁ ክፍል አንድ (አንቀፅ 1-3)</u>

በዚህ ክፍል በሌሎች ሕጎች ብዙም ያልተለመዱ እና ረቂቅ አዋጁን በአግባቡ ለመረዳት የሚያስችሉ ቃላትና ሀረጎች ትርጓሜዎች ተካተዋል (አንቀፅ 2)። በዚህም የትርጉም ክፍል“የግብርና ምርት”፣የእርሻ ምርት;“የግብርና

ምርት ውል"፣"አስመራች"፣"አምራች"፣"ግብይት ፣ የተማከለ፤መካከለኛ ሞዴል፤አውትግሮወርስ "የቴክኒክ ድጋፍ" እና ሌሎችም ቃላትና ሀረጎች እንዲተረጎሙ ተደርጓል።

የረቂቅ አዋጅ አንቀፅ 3 ደግሞ የረቂቅ አዋጁን የተፈፃሚነት ወሰን ደንግጓል።በዚህም መሰረት የአዋጅ ድንጋጌዎች በአንቀፅ2 (1) "የግብርና ምርት" እና የእርሻ ምርት፤ ተብለው በተወሰዱ የግብርና ምርቶች በሙሉና የግብርና ምርት ውል በዚህ አዋጅ በተሰጠው ትርጓሜ ውስጥ በሚወድቁ ማናቸውም ውሎች ተፈፃሚ እንደሚሆኑ ተደንግጓል።

## 2. <u>የረቂቅ አዋጁ ክፍል ሁለት (አንቀፅ 4-6)</u>

ይህ ክፍል ሰለግብርና ምርት ውል አመሰራረት ፣አፃፃፍና ሊይዛቸው ስለሚገባው ሁኔታዎች የተመለከቱ ድንጋጌዎችን ይዟል። በዚህም መሰረት እንደ ማንኛውም ውል የግብርና ምርትውል አመሰራረት የሚጀምረው በተዋዋይ ወገኖች በሚቀርብ የውል ሀሳብ (Offer) ሲሆን በድርድሩ ላይም ተዋዋይ ወገኖች በሦስተኛ ወገኖች በተለይም በመንግስት ተቋም ወይም በመንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች እገዛ ሊደረግላቸው ይችላል (አንቀፅ 4)። የውል ኃሳቡም በፅሁፍ ወይም በቃልሆኖ የውሉን ጉዳይ በበቂ ዝርዝር ማካተት ይኖርበታል (አንቀፅ 4) ።

የውሉን አፃፃፍ ፎርም በተመለከተም የግብርና ምርት ውል በፅሁፍ የሚደረግ ሆኖ ለተዋዋይ ወገኖች ግልጽና በማያሻማ አገላለፅ በመጠቀም መፈፀም ይኖርበታል (አንቀፅ 5)።ከዚህም በተጨማሪ የውሉን አፈፃጸም ለማሳለጥና አለመግባባቶችን ለመቀነስ የሚረዱ ተጨማሪ ግዴታዎች ተካተዋል። ውሉ ቢያንስ በሁለት ምስክሮች መረጋገጥ እንዳለበትና ከምስክሮችም አንዱ አግባብነት ያለው ባለስልጣን ተወካይ መሆን እንደሚኖርበት ተደንግጓል(አንቀፅ 5)። ከዚህ በተጨማሪም የተፈረመው የውል ቅጂ ውል ለመመዝገብ ሥልጣን በተሰጠው አካል መመዝገብ ይኖርበታል (አንቀፅ 5)። የግብርና ምርት ውል የግድ ሊያካትት የሚገባቸው ሁኔታዎችም በረቂቅ አዋጁ አንቀፅ 6 ተዘርዝረው ተቀምጠዋል።

## 3. <u>የረቂቅ አዋጁ ክፍል ሦስት (አንቀፅ 7-15)</u>

የረቂቅ አዋጁ ክፍል ሦስት የ<u>ምርት ውል ዓይነቶች፤</u> የአስመራቹን እና የአምራቹን አጠቃላይ <u>መብትና</u> ግዴታዎች፣ ስለዋጋ አወሳሰን፣ የክፍያ ዘዴ እና አከፋፈል፣ ሰለ ግብርና ምርቱ መጠን አወሳሰን፣ስለግብርና ምርቱ ጥራት አወሳሰን ፣ ሰለግብዓት አቅርቦት እና ክፍያ፣ የምርቱ የርክክብ ቦታ፣ ጊዜ እና የርክክብ ወጪዎቹን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን አካቷል ።

በዚህ አዋጅ የግብርና ምርት ውል አይነቶች ሁለት ናቸዉ ። አንድኛውአስመራች ከአምራቹ ጋር የሚዋዋለው የልማትና ምርት ግብይት ውል ሲሆን አስመራቹ ለአምራቹ ተፈላጊውን ግብዓት የማቅረብና የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት ግዴታየሚገባበት ነው። ሁለተኛው የውል አይነት ምርት ተጠቃሚ ኢንዱስትሪዎች፣አገልግሎት ሰጪዎችና ጅምላ ነጋዴዎች ከግብርና ምርት አምራቾች ጋር የሚደረግ የምርት ግብይት ውል ሲሆን አስመራቹ ለአምራቹ ተፈላጊውን ግብዓት የማቅረብና የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት በተዋዋይ ወገኖች ስምምነት ብቻ የሚወሰንበት ነው።

*በረቂቅ አዋጁ የአስመራቹ ግብዓት የማቅረብግዴታ በሁሉም የግብርና ምርት ውሎች ላይ አስገዳጅ መሆን አለበት ወይስ በተዋዋይ ወገኖች ስምምነት ብቻ የሚወሰን ይሁን የሚለው ጉዳይ አዋጁን በማርቀቅ ሂደት ወቅት በባለድርሻ አካላት ከፍተኛ ክርክር የተከሄደበት ነው ። ረቂቅ አዋጁን ያዘጋጁት ባለሙያዎች ግብአት ማቅረብ ግዴታ መሆን አለበት ብለው የሚያቀርቡት መከራከሪያ የዚህ ግዴታ መካተት አስመራቹ በምርት ሂደት ውስጥ መሳተፉን ለማረጋገጥ፣ የክህሎት ሽግግርን ለማሳለጥ እና የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ያስችላል በሚል ነው ። ይህ ግዴታረቂቅ አዋጁ ሊያሳካቸው ከታለመላቸው ዋነኛ ዓለማዎች ውስጥ በቀዳሚነት የሚጠቀስ ነው በማለት ሀሳባቸውን ያጠናክራሉ።አስመራቹ በምርት ሂደት የማይሳተፍበት ስምምነት በባሕሪው የእቃ ማቅረብ ውል ትኩረት ከፍተኛ ስለሚሆን ይህን አዋጅ ማውጣት ሳያስፈልግ አግባብነት ባላቸው የፍትሃብሔር ሕግ ድንጋጌዎች የሚገዛ ይሆናል ይላሉ ። በሌላ በኩል ደግሞ ግብአት ማቅረብ አስመራቹ ለአምራቹ ግብአት ማቅረብ ግዴታ መሆን የለበትም የሚሉት ወገኖች መከራከሪያቸው ግብአት ማቅረብ በሁሉምየግብርና ምርት ውሎች አስፈላጊ አይሆንም ፤አስፈላጊ ሆኖ ቢገኝም አስመራቹ ማቅረብ የማይችልባቸው ሁኔታዎች አሉ ብለው መከራከሪያ ነጥቦቻቸውን ያቀርባሉ።*

*የምርቶችን ዋጋ አወሳሰንን በተመለከተ ተዋዋይ ወገኖች የግብርና ምርቱን ጠቅላላ ዋጋ ወይም የነጠላ ዋጋ ክፍያ ሥሌት በግልጽ ማስፈር አለባቸው፤በውል ከተገለጸው የጥራት ደረጃ በመቀነስ ወይም በመጨመር ልዩነት ቢፈጠር የዋጋ ሥሌት ማስተካከያ በውሉ በግልፅ ማስቀመጥ አለባቸው።ተዋዋይ ወገኖች የግብርና ምርቱን ዋጋ አከፋፈል እና የክፍያ ጊዜ በገልፅ ማስቀመጥ አለባቸው።በግብርና ምርት ውል የልማትና ግብይት ግንኙነትን ዘላቂነት ለማረጋገጥ በምርት ርክክብ ጊዜ የምርት ገበያ ዋጋ በውል ከተገለጸው በላይ ከፍ ያለ እንደሆነ ሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች በድርድር የዋጋ ማሻሻያ ሊያደርጉየሚችሉበት ሁኔታ በረቂቅ አዋጁ ላይ እንዲካተቱ ተደርጓል (አንቀፅ* 10)።
*የረቂቅ አዋጁ ክፍል ሦስት፤ ካካተታ*<u>(*አንቀፅ* 17- 21)</u>*ቸው ድንጋጌዎች ሌላው ከግብርና ምርት ውል የሚመነጭ መብትና ግዴታ ሰለሚተላለፍበት ሁኔታ ነው። በዚህም መሰረት በውሉ በሌላ ሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር ተዋዋይ ወገኖች ከውሉ የሚያገኙዋቸውን መብቶች ለሦስተኛ ወገኖች የማስተላለፍ ነጻነት ሲኖራቸውግዴታዎችን ለማስተላላፍ የሚችሉት ግን የሌላኛውን ተዋዋይ ወገን ይሁንታ ካገኙ ብቻ ነው (አንቀፅ* 16)።

4. <u>***የረቂቅ አዋጁ ክፍል አራት***</u>

*ተዋዋይ ወገኖች በተለያዩ ምክንያቶች የውል ግዴታቸውን ላይፈፅሙ ይችላሉ። ይህ ሲሆን አግባብነት ያላቸው የፍታብሔር ሕጎች ተፈፃሚ ሊሆኑ ይችላሉ። በተለይም ተዋዋይ ወገኖች ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የውል ግዴታቸውን ለመፈፀም ሊቸገሩ ይችላሉ። ረቂቅ አዋጁ በአንድ በኩል ከአቅም በላይ የሆነ ሀይል ሊባሉ የሚችሉ ክስተቶችንና ውጤታቸውን በውላቸው የመወሰን ስልጣን ለተዋዋይ ወገኖች የሰጠ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ከአምራቹ በኩል በማንኛውም ሁኔታ ከአቅም በላይ ተብለው ሊወሰዱ የሚገባቸውን ክስተቶች ለይቶ አስቀምጧል*

(አንቀፅ 17(1) ።ይህም ውሉ ያልተፈፀመው ከአቅም በላይ በሆነ ክስተት ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ክርክር ከወዲሁ ለመቀነስ ያስችላል ተብሎ ይታመናል።እንዲሁም የመድህን ዋስትናን የተመለከቱ ድንጋጌዎችም ተካተዋል(አንቀፅ 18)፡

5. **<u>የረቂቅ አዋጁ ክፍል አምስት (አንቀፅ 19 -20)</u>**

*ይህ የረቂቅ አዋጁ ክፍል የውሉ ዘመን የሚወሰንበትን ሁኔታ* (*አንቀፅ* 19)፣*<u>ውሉን ስለማሻሻል ወይም ስለመቀየር</u> የሚቻልባቸውን መንገዶች* (*አንቀፅ* 20) *እና ውሉ<u>ስለሚቋረጥበት</u> ሁኔታዎች* (*አንቀፅ* 21) *የያዙ ድንጋጌዎችን* አካቷል።

6. **<u>የረቂቅ አዋጁ ክፍል ስድስት (አንቀፅ 22)</u>**

*ይህ የረቂቅ አዋጁ ክፍል አለመግባባቶች ሲከሰቱ የሚፈቱበትን ስረዓት ይደነግጋል። ከግብርና ምርትውልልዩ ሁኔታዎች ጋር የሚስማማ ያለመግባባቶች መፍቻ መንገድ ያስፈልጋል። በአንድ በኩል ሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች መደበኛውን የፍትህ ስርአት ለመጠቀም እኩል እድል ላይኖራቸው ይችላል። በሌላ በኩል ደግሞ ውሉ ለረጅም ጊዜ የሚቀጥል ሊሆን ስለሚችል አለመግባባቶች የሚፈቱበት መንገድ የተዋዋዮችን የወደፊት መልካም ግንኙነት የማይጎዳ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።*

*በረቂቅ አዋጁ የተካተቱት አለመግባባትን ስለመፍታት የተደነገጉት ድንጋጌዎች በዚህ መንፈስ የተቃኙ ናቸው።ከዚህ አንፃር አለመግባባት ሲነሳ ተዋዋይ ወገኖች በራሣቸው በመወያየት እና በመደራደር ለመፍታት መሞከር ይኖርባቸዋል። ተዋዋይ ወገኖች አለመግባባቱን በራሣቸው በመወያየት እና በመደራደር መፍታት ካልቻሉ ለሦስተኛ ወገን ግልግል በማቅረብ ሊፈቱት እንደሚችሉ ተደንግጓል ። በግልግል መፍታት ካልቻሉ ደግሞ በሽምግልና ዳኝነት ወይም በፍርድ ቤት መፍታት ይችላሉ ።*

7. **<u>የረቂቅ አዋጁ ክፍል ሰባት (አንቀፅ 23)</u>**

*ይህ የረቂቁ አዋጁ ክፍል የግብርና ምርት ውሎችን ለማስተዋወቅ፣ ለማስፋፋትና ለማስተባበር የሚያስችል ተቋማዊ ስልጣንና ተግባር የሚወስን ነው። በአገራዊ ደረጃ የግብርና ምርትውሎችን የማስተዋወቅ፣ የማስፋፋትና የማስተባበር ኃላፊነት የተሰጠው ለግብርና ሚኒስቴር ሲሆን የሚኒስቴሩ ዝርዝር ስልጣንና ተግባራትተለይተው ተቀምጠዋል።ስልጣንና ተግባራት በዋነኛነት ለሚኒስቴሩ የተሰጡ ቢሆንም ኃላፊነቱን ለመወጣት ይቻለው ዘንድ ሚኒስቴሩ ከሌሎች አግባብነት ካላቸው ከፌዴራልና ከክልል የመንግስት ተቋማት ጋር በትብብርና በቅንጅት መስራት እንደሚኖርበት ተደንግጓል።*

*በክልል ደረጃ የግብርና ምርት ውሎችን የማስተዋወቅ፣ የማስፋፋትናየማስተባበር ስልጣንና ተግባራትየሚሰጠውአካል አግባብነት ባለው ክልል እንደሚሰየም ተደንግጓል።*

8. **<u>የረቂቅ አዋጁ ክፍል ስምንት(አንቀፅ24-26)</u>**

ይህ የረቂቅ አዋጁ ክፍል ልዩ ልዩ ድንጋጌዎችን አካቷል። ተፈጻሚነት የሚኖራቸውን ሕጎች (አንቀፅ 24)፣ተፈፃሚነት የማይኖራቸውን ሕጎች (አንቀፅ 25) ወዘተ የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ተካተዋል።